# በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሠልጠኛ ተቋም እና በሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር MGIMO ዩኒቨርሲቲ ጋር ተባብሮ ለመስራት የትብብር ስምምነት ተፈረመ።



በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሠልጠኛ ተቋም እና በሩሲያው **Moscow State Institute of International Relations** (MGIMO) ዩኒቨርሲቲ መካከል የመግባቢያ ሰነድ እ.ኤ.አ. ፌብሩዋሪ 17/2017 ሞስኮ ውስጥ ተፈርሟል። ስምምነቱ ሁለቱ ተቋማት በዲፕሎማሲ፣በአለምዓቀፍ ግንኙነት እና ተዛማጅ መስኮች የምርምር ሥራዎችን በጋራ ለመስራት፣ በዋናነትም በዲፕሎማቶች ሥልጠና፣በመምህራን ልውውጥ፣የጥናትና የምርምር ስራዎችን በጋራ ለማካሄድ የሚያስችላቸው ነው።

በኢትዮጵያ በኩል ስምምነቱን የፈረሙት ክቡር አምባሳደር ግሩም አባይ በሩሲያ ፌዴሬሽን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ልዩ መልዕክተኛና ባለ ሙሉ ስልጣን አምባሳደር ሲሆኑ፣ከሩሲያ ወገን ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ሬክተር Mr. Anatoly V.Torkunov ናቸው።



ስምምነቱ በሁለቱ ተቋማት መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲመሰረት፣በዚሁም በሰነዱ የተካተቱት የትብብር መስኮች በአግባቡ እንዲከናወኑ ሕጋዊ መነሻ የሰጠ ሆኖ ይገኛል።

ይህ ስምምነት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥር የተቋቋመውን የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሠልጠኛ ተቋምን አቅም ለማሳደግ እና የሚኒስቴር መ/ቤቱን የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ፕሮግራም ተፈጻሚ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲሚኖረው ይታመናል።

በዛሬው እለት የተፈረመው ይኸው የመግባቢያ ስምምነት በኢትዮጵያና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል ያለውን ዘርፈ ብዙ የትብብር ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር የበኩሉን አስተዋጸኦ የሚያበረክት መሆኑ ታምኖበታል።


